# ሀገራዊ ልዑላዊነት
# ክብረት

H.R. 2003 THE TEMPTATION OF OUR ERA/ የዘመናችን ታላቁ ፈተና

ጀግኖቹ አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ከሩቁም ከቅርቡም የሚነሱባቸውን ጠላቶች፣ ቅኝ ገዢዎችን ሁሉ ገና ከርቀ አረማመዳቸውንና ተንኮላቸውን ጠንቅቀው በመገንዘብ <<ወግድ! አትቅረቡን፥ አትንኩን፥ እምቢ ለነጻነታችን>> በማለት አጥንታቸውን ከስክሰው፥ ደማቸውን አፍስሰው፥ ውድ የሕይወት መስዋዕት እየከፈሉ፣ ክብሯን እና ዳር-ደንበሯን ጠብቀው፣ ልዑላዊትና ነጻ ሀገር አስረክበውናል። ነገር ግን በዚህች ከአቦቶቻችን የወረስናትን በቅኝ ግዛት ያለመገዛት፣ ለዘመናት በነጻነትና በልዑላዊነት በመኖራችን ብቻ የሚቀኑብን በጣም ብዙዎች ናቸው። ወደዳችሁም ጠላችሁም፣ ምድረ ፈረንጅ በሙሉ ይህችን ነገር ሊሰሟት አይወዱም፣ ይቀኑብናል። በቅኝ ግዛት ያልተነካች ድንግል ሀገር፣ ይህች ምድረ ሓበሻ ሳትራከስ እንዴት አመለጠች? በማለት ቍጨት አለባቸው። ዋናው ነገርም ኢትዮጵያ የኤውሮጳው የትምክሕት ኃይል ቀንበር የሰበረ፥ ፈረንጅን ያሳፈረ ሕዝብ በመሆኑም ለእነርሱ የማይረሳ ቂም ነው፤ መግቢያ ቀዳዳ ቢያገኙም ምን ጊዜም ቢሆን ኢትዮጵያን ከመበቀል አያርፉም፤ ይህችን አትርሱ። ለምሳሌ H.R. 2003 ይህነን እምቢ አልገዛም ባይነት መንፈስ ለመቀልበስ የተውጠነጠነና የዘመኑ ኢትዮጵያዊ ትውልድ የጥንት አባቶቹን አትንኩኝ ባይነት ሱሪ መታጠቁን ወይም ያለመታጠቁን ለመፈታተን የመጣ ጣጣ ወይ ክፉ ፈተና (EVIL *TEMPTATION*) ነው። H.R. 2003 ከኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በላይ የበላይ ሕግና ተቆጣጣሪ ሆኖ እንዲሠራ የታቀደ ፀረ ልዑላዊነታችን ነው። ልዓላዊነት ደግሞ መደፈር የማይገባው የሕዝቦች ክብር ነው።

የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራን በ*STANFORD UNIVERSITY "ENCYCLOPEDIA OF PHILOSOPY"* መዝገብ፣ ለትምህርትና ለታሪክ በሚበጅ መልኩ፣ ስለ ልዑላዊነት *(Sovereignty)* ሰፊ ሓተታ ዘግበዋል። እኔም ከሓተታው የተዋስኳትን ቁም-ነገር ለአንባብያን ባካፍል መልካም ነው በሚል መሠረተ ሓሳብ ይህችን ጽሑፍ አበረክታለሁ። ልዑላዊነትን መነሻ አድርጌ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ወቅታዊ ሁኔታ ደግሞ የዩናትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካን፣ ታችኛው ምክር ቤት ያወጣው፣ *H.R. 2003, the Ethiopian Democracy and Accountability Act of 2007* የተባለው ረቂቅ ሕግ ያስከተለውን ግርግር ቀልቤን ስለሳበው ነው። በዓይነ ህሊና ረቂቅ ሕጉን ስመለከተው ደግሞ ለአሜሪካም ሆነ ለኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ፋይዳ አላየሁበትም። እንዲያውም H.R. 2003 በሚፈጥረው ጫና ምክንያት እያደር የአሜሪካ ጥቅም ይጎዳል፤ በወዳጆቿም እምነት ታጣለች ባይ ነኝ።

የኢትዮጵያ ሕዝብም H.R. 2003 በልዑላዊነቱ ላይ የተነጣጠረብኝ ረቂቅ አዋጅ ነው ብሎ እንዃ በሀገር ደረጃ ተችቶበታል፤ ተቀባይነትም የለውም።

ስለሆነም *H.R. 2003* ሁለንተናው በጉድፍ የተሞላ፥ ሕገ-ወጥ፣ ቅኝ ግዛታዊ፣ አሳዛኝና አሳፋሪ ረቂቅ አዋጅ ሆኖ ይታየኛል። እናም፦ እኔም ይህነን ግንዛቤና አቋም በጽሑፍ መልክ ግልፅ ለማድረግ፣ እንዲሁም ሰምቼ እንዳልሰማሁ፣ አይቼም እንዳላየሁ ዝም ከማለት ይልቅ የሞራል ግዴታየንም ለመወጣት ነው። በቅድሚያ ግን ስለ ሀገራዊ ልዑላዊነትና ትርጉሙ ብንወያይና ብንማማር ጠቃሚ መስሎ ይታየኛል። ምክንያቱም <<ያላወቁ እየተናነቁ አለቁ>> እንዲሉ፣ ካለማወቃችን የተነሳ እንዳንነሳሳት፣ ክብራችንና ልዑላዊነታችንን አሳልፈን እንዳንሰጥ ይረዳናል። የምንደግፍበትንና የምንቃወምበትን ፍሬ-ነገር ለመለየት ይጥቅመናል። ሀገራዊ ልዑላዊነት ማለት ምንማለት እንደሆነ ማወቅ በሀገራዊ ልዑላዊነታችን ላይ ከሚፈታተነን *የዘመናችን ክፉ ፈተና* (Immense Temptation)፣ ከ*H.R. 2003 ጉዳቱን* አውቀን ለመጠንቀቅ ያስችለናል ማለት ነው። ዋናው መልእክቱ በዲሞክራሲና በተጠያቂነት ከለላ ልዑልነታችንን፣ ክብራችንን አናስደፍር ለማለት ነው።

**ስለ ልዑላዊነት ከምሁራኑ የተገኘው አስረጅ፡-** I found an interesting article from Stanford University's website, "Encyclopedia of Philosophy," on sovereignty. According to the Encyclopedia, "*sovereign* is the supreme lawmaking authority, subject to no other." I could not find any exception that allows violation of any country's sovereignty in the name of democracy or accountability. In the same article, Stanford University says: "Sovereignty is the exclusive right to exercise political power and to have complete control over an area of governance, people or geographical area." Further more, the article says, "a government is considered sovereign if it has the final word on political decisions within its boundaries. When citizens can appeal to a higher body, the government is not sovereign." **ቅንጅቶች በዋሽንቶን እንዳደረጉት ዓይነት ማለት ነው።** We also know that States and local governments in the United States have a great deal of power, but ultimately they are not sovereign, because the federal government can overrule them. This defines the limits that the states and local governments have. This means Subordinates do not have the final say and "there is no law without a sovereign።" **ይላል። በበለጠም በ**(*http://en.wikipedia.org/wiki/Sovereign*) ***ገቡና እዩ።***

***አዎ! የንጉሥ ያለህ! ይግባኝ የሚሉበት፣ የበላይ ዳኛና ተቆጣጣሪ ባለበት ሁሉ ብሔራዊ ክብር፣ ነጻነትና ልዑላዊነት ብሎ ነገር የለም። ስለዚህ*** *H.R 2003 treats Ethiopia as a subordinate State to the American government; H.R 2003 violates the sovereignty of Ethiopia. Ethiopia is not the United States' subordinate State.* ***ታድያ፣*** H.R 2003 ***ብሎ ሕግ አውጥቶ በዚህ ግቡ በዚህም ውጡ፤ ከዚህ እንዳታልፉ፤ የሠራችሁትንም ሁሉ ወደ እኛው ሪፖርት አቅርቡ ብሎ ለማዘዝ መሞከር ድፍረት ነው ከማለት ውጭ ሌላ ስም ሊወጣለት አይቻልም። በልዑላዊነታችን እና በብሔራዊ ክብራችን ላይ በተቃጣ ድፍረት ከመደፈር የከፋ ደግሞ ሌላ ዓይነት ጉዳት ከቶ ሊኖር አይችልም። በተለይ*** *A sovereign is the supreme lawmaking authority, subject to no other* ***በሚል ከዚህ በላይ በተሰመረበት መሠረተ ሓሳብ ላይ ተንተርሰን*** H.R 2003***ን ስንመረምረው አሳፋሪና አሳዛኝ ረቂቅ አዋጅ ከመሆኑም በላይ በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታና እውነታ ያላገናዘበ፣ ጅምሯን ዲሞክራሲ የሚያጨልምና ሰላሟን የሚያናጋ ረቂቅ አዋጅ ነው። ያልሰማ ይስማ፣ የሰማ ደግሞ ላልሰማ ያሰማ፣*** H.R 2003 ***በልዑላዊነታችን ላይ የተሰነዘረ፣ ቅኝ ግዛታዊ ረቂቅ አዋጅ ነው።***

***የአሜሪካ ምክር ቤት በሉዑላዊት ሀገር፣ በኢትዮጵያ ላይ ልዑላዊንቷን በመተላለፍ፣*** *H.R. 2003, the Ethiopia Democracy and Accountability Act of 2007* ***የሚል ረቂቅ ሕግ በማውጣት በሰነዘሩት ድፍረት እኔ በአሜሪካዊነቴ አፍሬባቸዋለሁ፣ በኢትዮጵያዊነቴ ደግሞ አዝኜባቸዋለሁ። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ድፍረትና መተላለፍ ከዚህ ከታላቁ ሀገረ አሜሪካ ምክር ቤት ሊወጣ ቀርቶ ሊታሰብም የማይችል ያልተጠበቀ ዱብ ዕዳ ነው፤ እናም ያሳፍራል፣ ያሳዝናልም። ስለዚህ <<የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም>> እንዲሉ፣ እኔም የረቂቅ አዋጁ ጎጂነት፣ አሳፋሪነትና አሳዛኝነት ላላወቁ ለማሳወቅና ጉዳቱ ምን ላይ ነው በማለት ለሚጠይቁ ወገኖች ለማስረዳት እሞክራለሁ።***

***ይህ ረቂቅ አዋጅ በኢትዮጵያ ልዑላዊነት ላይ የተሰነዘረ የወጣለት ቅኝ ግዛታዊ ረቂቅ አዋጅ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ማለትም ከዚህ በላይ በምሁራኑ መረጃ በተደገፈው ዝንተ ሙግታዊ ትርጓሜ/***Definition ***መሠረት የልዑላዊነትን ትርጉም መረዳት ከተቻለ፣ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ልዕልና በረቂቅ ሕጉ መደፈሩ አያጠያይቅም። በመሆኑም የ***H.R 2003 ***ጉዳት ምኑ ላይ ነው እያሉ ለሚጠይቁ ወገኖች ይህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ማለት።***

***፩ኛ. ይህንን ረቂቅ አዋጅ ያወጡት የአሜሪካን ምክር ቤት አባሎች በማያገባቸው ቦታና ሁኔታ ላይ ጣቶቻቸውን ሲቀስሩና ያልተወከሉበትን ነገር ሲሠሩ***

ማየት ያሳፍራል፣ ያሳዝናልም። ምክንያቱም የምክር ቤቱ ውክልና ለአሜሪካ ሕዝብ እንጂ ለኢትዮጵያ ወይም ለማንኛውም ሌላ ሀገር አይደለም። የአሜሪካ ሕዝብ ሰነተሮቹን/Senators ለኢትዮጵያውያን የሚሆን ሕግ አውጡ ብሎ ውክልና አልሰጧቸውም ማለት ነው። እንዲያውም ይህ በሰው ቤት ገብቶ ማበጣበጥና ጣልቃ ገብነት ስለሆነ፣ የአሜሪካ ወዳጅ ሀገሮችን አንድ በአንድ የሚያገልልና ፀረ አሜሪካም ፀረ ኢትዮጵያም ነው። አዋጁ ሁሉምንም የሚጎዳና የሚያሳፍር ክፉ ፈተና Enticement ነው።

፪ኛ. በምክር ቤቱ ጉዳዩ በሚገባ ሳይመረመርና የሚያስከትለውን የዲፕሎማሲ ችግር ግምት ውስጥ ሳያስገቡ፣ በእከክልኝ ልከክህ መልኩ ረቂቅ ሕጉን በችኮላ ማሳለፋቸው ደግሞ ይበልጥ አሳፋሪ ያደርገዋል። እንዲሁም ከግምት በታች ወርደው በጥቂት የቀድሞ የደርግ ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዲስት ኮሚሳሮችና ካድሬዎች ውትወታ፣ የአሜሪካ ምክር ቤት እንዲሁ በቀላሉ *(Easily manipulated and mislead)* መትተታቸውና መታለላቸው ያሳፍራል፥ ያሳዝናልም። እንደዚሁም የማይመለከታቸውን ሥራ በመሥራት የአሜሪካ መንግሥታዊ አሠራር ለዓለም አቀፍ ትዝብት መጋለጣቸውም ያሳፍራል። H.R 2003ን በውል ለተገነዘበው ዜጋ ሁሉ በአንድ ድሃ አገር ላይ የተሰነዘረ ጥቃትና በልዑላዊነቷ ላይ የተቃጣ በደል/ፈተና በመሆኑ ያሳዝነዋል። እኔ ኢትዮጵያ ተወልጄ ያደኩባት፣ እትብቴ የተቀበረባት አገሬ ናት። አሜሪካ ደግሞ በፈቃዴ ዜጋ የሆኑሁባት መኖሪያየና ሀገሬ ናት፤ እናም፣ አሜሪካና ኢትዮጵያ ወዳጅ ስለሆኑ ምክር ቤቱ የሰነዘረው ድፍረት ወዳጅነቱን የሚያሻክር በመሆኑ አሳዝኖኛል።

፫ኛ. በሀገሩ (በኢትዮጵያ) ያለውን የረዥም ጊዜ የነጻነትና የታሪክ ባለቤት የሆነው ሕዝብ ንቃተ ህሊና ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ የልዑላዊው ሕዝብ፣ የመንግሥትና የሀገር ክብር የተዳፈረ ረቂቅ አዋጅ በመሆኑ አሳዝኖኛል። ምክንያቱም ይህ ድፍረት ነው ከሚል መገለጫም ባሻገር፣ የኢትዮጵያ ሀገራዊ መንግሥታዊ ክልል ወይም ዳር-ድንበሯን ዘሎ ልዑላዊነቷን ከተዳፈረው ከሻዕቢያ መንግሥት በላይ ወይም ከጥንቱ ጠላት፣ ጣሊያን ከባሕር ማዶ መጥቶ ልዑላዊት ሀገር፣ ኢትዮጵያን እንደወረራት ያክል ነው የሚተረጎመው። እንዲያውም ይህ ቅኝ ግዛታዊው ረቂቅ አዋጅ ከተጠቀሰው ድፍረት በላይ የላቀ የኢትዮጵያ ሁለተናዊ የነፃ ሕዝቦች ክብርና ልዕልና ላይ የተሰነዘረ *"ወራሪ አስተሳሰብ"* ነው ተብሎ ቢተረጎምም ያስኬዳል የሚል እምነት አለኝ። ይህንን አመለካከትም ብዙ ሕዝብ የሚጋራው እውነታ ነው። እሱም፡- አዎ! H.R 2003 ድህነት ጎትቶ ያመጣልን ***"ቅኝ ግዛታዊ ፈተና"*** ነው የሚል ነው።

፬ኛ. ከማፈርና ከማዘንም በላይ አስግርሞኛል። ምክንያቱም የአሜሪካን ወዳጅ በሆነችው በልዑላዊት ሀገር፣ በኢትዮጵያ ላይ የተቃጣው ቅጥ አልቦ ድፍረት በወታደራዊ ኃይል በተወረሩት በአፍጋኒስታንና በኢራቅ ላይ እንኳን ያልተፈጸመ ድፍረት ነው። በአፍጋኒስታንና በኢራቅ የተደረገው ከዚህ በዓይነቱ የተለየ፣ ዓለም አቀፋዊ ሕግና ዲፕሎማሲያዊ ሥርዓት የተከተለ፣ የሕዝቦቹ የተፍጥሮ ነጻነትና ሀገራዊ ልዑላዊነትን ባልተዳፈረ መልኩ ነው የተፈጸመው። ማለትም መንግሥታት እንዲመሰረቱና የየራሳቸው ሕገ መንግሥት እንዲያረቁ ነው የተደረገው እንጂ በአሜሪካ ምክር ቤት H.R ተብሎ ሕግ ትረቆ አልተላከላቸውም። ለምሳሌ በኢራቅ በተዋቀረው አዲሱ መንግሥት፣ ኢራቃዊ ሕግ አርቃቂ ክፍል የራሱ ሕገ መንግሥት እንዲረቅ ተደረገ እንጂ በአሜሪካውያኑ ምክር ቤት ተረቆ ወደ ኢራቅ የሕግ ጦማር አልተላከላቸውም። በአፍጋኒስታንም እንዲህ ዓይነቱ ድፍረት የተሰነዘረ አይመስለኝም።

፭ኛ. ኢትዮጵያን በሚመለከት ግን አንድ ልዩ አሳፋሪና አሳዛኝ መልክ አስይዞውታል። ከዚህ በላይ በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደተሞከረው፣ የአሜሪካ ሕግ አውጪዎች ለኢትዮጵያና በኢትዮጵያ የሚያገለግል

ሕግ ነው የተረቀቀው። የረቂቁ ስምም H.R 2003 የሚል ነው። ትርጉሙም፡- *House Resolution 2003* ለኢትዮጵያ የሚያገለግል የሜሪካ ምክር ቤት ያወጣው የሕግ ረቂቅ አዋጅ ማለት ነው። እንዲህ ማድረግ ማለት ደግሞ ሕግና ሥርዓት ተላልፈው በኢትዮጵያ ያለውን ሕግ አውጭና ሕግ አስፈጻሚው መንግሥታዊ አካል ሕዝብም ጭምር ሁሉም እንደሌሉ አድርጎ እንደ ማሰብና ማሳነስ ማለት ነው። መኖራቸው ቢታመንም የራሳቸውን ሕግና ሥርዓት መውጣት አይችሉም ብሎ የሕዝቡ ንቃተ ህሊና፣ ነፃነት፣ ክብርና ሀገራዊ ልዑላዊነትን መናቅ ማለት ነው። ይህ ረቂቅ አዋጅ በማያገባው በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳዮችም ጣልቃ ገብቶ ይዘባርቃል። ለምሳሌ በምርጫ ቦርድ ሥራ ላይ፣ ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ እና በተቃዋሚ ድርጅቶችና በመንግሥት መካከል ሊኖር የሚገባውን አሠራርና ግኑኝነትን በተመለከተ ረቂቅ ሕጉ ጣልቃ ይገባል። የሀገር ሕገ-መንግሥትን ይጥሳል፤ አሻሽሉት (Revise it) እስከ ማለት ይሄዳል። ይህንን መደገፍ ራሱ ሀገራዊ ክሕደትና ውርደት ነው። ልዑላዊነት የዳር ድንበር ጥበቃ ብቻም አይደለም። የዲሞክራሲ፣ የነጻነት፣ የሕግና የሰብአዊ መብት ጥያቄዎችንም ያካትታል። ሀገራዊ ልዑላዊነት ከተጣሰ ሀገራዊ ክብር የለም፥ ህሉም የሉም። *Patrick Henry, March 23, 1775."Give Me Liberty Or Give Me Death*" ሲል የጮሆው ሰለራሱ የግል ነጻነቱ ሳይሆን ስለ ልዑላዊት አሜሪካ ነበር፤ በልዑላዊነት ዋዛ አያስፈልግም።

H.R 2003 የተባለው ረቂቅ አዋጅ የተረቀቀው ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ የሚላከውን እርዳታ እንዴት ሥራ ላይ እነደሚውል ለማወቅ ነው፤ H.R 2003 የኢትዮጵያ ክብርና ልዑላውነትን አልተዳፈረም፤ የሚሉ የዋሆች አልታጡም። ነገር ግን ይህ የእርዳታ መስጠትና ያለመስጠት ወይም የሰጠናችሁ እርዳታ የት ይውላል ለማለት አይደለም። በሰብአዊነት የተቸረና እርዳታን ብቻ የሚመለከት ቢሆን ኖሮ፣ በቀላሉ በመመካከር የሚፈጸም የበጎ አድርጎት ተልእኮ/Humaiterian Mission ነው እንጂ በምክር ቤት ደረጃ ረቂቅ ሕግ ወይም የወረተኝነት አዋጅ ማውጣት የሚያስፈልገው ጉዳይ ሊሆን አይችልም። እሱም ካመኑበት ለመስጠት ካላመኑበት ደግሞ ላለመስጠት ወይም ለማቆም በራሳቸው የውስጥ አሠራር የሚያልቅ መሆን ነበረበት ማለት ነው። H.R 2003 ግን ከዚህ በተለየ መልኩ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ክብርና ነፃነት ላይ የተሰነዘረ ፈተና/ Temptation ነው።

H.R 2003 ሕግ ሆኖ ቢወጣ፣ የአሜሪካና ኢትዮጵያ ወዳጅነትና አጋርነት ከማቀዝቀዙም በላይ የዲፕሎማሲ ግንኙነታቸውን የጌታና የሎሌ መልክ ሊያስይዘው ይችላል ማለት ነው። ኢትዮጵያውያ ሕዝቦች ደግሞ ይህነን የመቀበል ልምድ፣ ታሪክ ወይም ፍላጎት የላቸውም። በ*Unted states House Resolution* ደረጃ፣ ኢትዮጵያ በእርዳታ መከልከል ዛቻ ወይም ማስፈራርያ ተገዳ የምትቀበለው ሕግ ማውጣት ማለት ደግሞ ለራሱ ችግር አለው። ማለትም አሜሪካ በወዳጆቿ ላይ እንዲህ የምታደርግና ወረተኛ ሀገር ከሆነች፣ ሌሎች ሀገሮች እምነት ያጡባታል ማለት ነው። ምክንያቱም ወዳጅ መሆን እንዲሁ ለጥቃት የሚያጋልጥና የሚያስደፍር ከሆነ፣ ኢትዮጵያን አይተህ ተቀጣ፥ የአሜሪካ ወዳጅነት በሩቁ፣ በማለት ብዙ አገሮች ከአሜሪካ ሊርቁና ሊሸሹ ይችላሉ የሚል ጥርጣሬ ሊያስከትል ይችላል። የአሜሪካ ምክር ቤት ይህንን ታላቅ ስሕተት እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳቶችን ያለመመልከታቸው ራሱ የሚያስገርም፣ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው። እኔ በኢትዮጵያዊ አሜሪካዊነቴ አሳፍሮኛል፥ አሳዝኖኛልም። አዎ! (H.R. 2003 IS THE TEMPTATION OF OUR ERA)፣ ማለትም ድህነት ጐትቶ ያመጣልን የዘመናችን ታላቁ ቅኝ ግዛታዊ የበላይ አዛዥ፣ በዚህ ግቡ፥ በዚህም ውጡ የሚል፣ በሰው ቤት ገብቶ አጋፋሪ ልሁን የሚል፣ ዓይን አውጣ ወራሪ አስተሳሰብ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ትጉም የለውም።

12/29/2007 ወይም ታኅ. ፳፩ ቀን፥ ፳፻ ዓ/ም።